# ርቱዕ እና ኢ-ርቱዕ ወደረኝነት

1. አንድ መኪና በተመሳሳይ ፍጥነት እየተጓዘ በ 3 ሰዓት 120 ማይልስ ከተጓዘ 200 ማይልስ ለመጓዝ ስንት ሰዓት ይወስድበታል?
2. የአንድ መጽሃፍ 4 ገጾችን አንብቦ ለመጨረስ 18 ደቂቃ ከወሰደ የመጽሃፉን 30 ገጾች አንብቦ ለመጨረስ ስንት ደቂቃ ይወስዳል?
3. አንድ ባለሱቅ 25 ሳጥኖችን አሽጎ ለመጨረስ 2 ሰዓት ቢወስድበት በ 8 ሰዓት ውስጥ ስንት ሳጥኖችን አሽጎ ይጨርሳል?
4. 13 ሳሙና 26 ግራም ይመዝናል ፡፡ 35 ሳሙናዎች ስንት ግራም ይመዝናሉ?
5. አንድ ኬክቤት 30 ዶናቶችን በ 60 ደቂቃ ካመረተ 120 ዶናቶችን ለማምረት ስንት ደቂቃ ይወስድበታል?
6. 7 ኩኪሶች ለመስራት 3 እንቁላል ያስፈልጋል ፡፡ 14 ኩኪሶችን ለመስራት ስንት እንቁላል ተጨማሪ ያስፈልጋል?
7. አንድ 540 ግራም የሚመዝን ቶርታ ኬክ ለመስራት 180 ግራም ስኳር ያስፈልጋል ፡፡ 5400 ግራም ቶርታ ኬክ ለመስራት ስንት ግራም ስኳር ያስፈልጋል
8. አንድ ጭልፊት በሰዓት 15 ኪሎሜትር የሚበር ከሆነ 180 ኪሎሜትር ለመብረር ምን ያህል ሰዓት ይወስድበታል?
9. ሃ እና ለ ርቱዕ ወደረኛ ቁጥሮች ናቸው፡፡ ሀ 21 ሲሆን ለ ደግሞ 14 ይሆናል፡፡ የ ሀ ዋጋ 201 ሲሆን የለ ዋጋ ስንት ይሆናል?

LIVEWORKSHEETS

10. አንድ መኪና የሚጠቀመው ነዳጅ እና የሚጓዘው ርቀት መካከል ያለው ግንኙነት ርቱዕ ወደረኛ ቢሆን ፣ መኪናው በ 20 ጋሎን ነዳጅ 500 ማይል ርቀት ቢጓዝ የወደረኝነት መጣኙ ስንት ይሆናል ?

11. ሸ እና ቀ ኢ ርቱዕ ወደረኛ ናቸው ። ሸ 45 ሲሆን መጣኙ ቁጥር ደግሞ 5 ነው ። ከሚከተሉት ውስጥ የ ሸ እና የ ቀ ጥንድ ቁጥሮች ሊሆኑ ይሚችሉት የትኞች ናቸው ?

ሀ) ( 45 ፣ 9 ) ለ) ( 10፣ 2) ሐ) ( 35፣ 7 ) መ) ሀ እና ለ

12. 12 የግንበኛ ሰራተኞች አንድ አነስተኛ ቤት ገንብተው ለመጨረስ 10 ቀናት ቢወስድባቸው 5 የግንበኛ ሰራተኞች ስንት ቀናት ይወስድባቸዋል?

13. አንድ ቧንቧ የግቢያችንን አታክልቶች ለማጠጣት 60 ደቂቃ የወስድበታል ? 6 ቧንቧዎች ብንጠቀም በስንት ደቂቃ አጠጥተን መጨረስ እንችላለን?

14. አንድ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ 150 ሰዎችን ቢቀጥር ሥራውን በ 30 ቀናት ማጠናቀቅ ይችላል። ሥራውን በ 20 ቀናት ለማጠናቀቅ ቢፈልግ ስንት ተጨማሪ ሰራተኞች ያስፈልጉታል?

15. ሀ እና ለ ኢ ርቱዕ ወደረኛ ቁጥሮች ናቸው ። የ ሀ ዋጋ 3 ሲሆን ለ ደግሞ 20 ይሆናል ፣ የ ሀ ዋጋ 12 ሲሆን ለ ስንት ይሆናል?

16. ሀ እና ለ ኢ- ርቱዕ ወደረኛ ቁጥሮች ናቸው ። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ላይ ለ 20 ሲሆን ሀ ስንት ይሆናል?

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ | 5 | 10 | ?? |
| ለ | 60 | 30 | 20 |

ሀ) 25 ለ) 15 ሐ) 25 መ) 5

LIVEWORKSHEETS

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ርቱዕ እና ኢ ርቱዕ ወደረኛ የሆኑትን ለዩ

17. የምናደርጋቸው የሰውነት እንቅስቃሴዎች እና ሰውነታችን የሚያቃጥለው ካሎሪ መጠን

18. በውስጣችን የሚፈጠር የፍርሃት መጠን እና የልብ ምታችን ፍጥነት

19. የምንሰራው ስራ እና ሰውነታችን ላይ የሚፈጠረው የድካም መጠን

20. በቤታችን ውስጥ የምንጠቀመው የመብራት እና የውሃ ፍጆታ ከምንከፍለው ወርሃዊ የገንዘብ መጠን ጋር ያለው ግንኙነት

LIVEWORKSHEETS